# የኢሳት ጉዳይ፡- 17102020

(ጋዜጠኛ ምናላቸው ስማቸው)

ይህ ሚዲያ ሀገርን ከወያኔ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የከፈለው መስዋዕትነት አሌ የሚባል አይደለም።

ኢሳት በቀደምት ስራው እኔን ጨምሮ ለብዙዎች ድምፅ የመሆኑን ያህል የስልጣን ጥመኞች የፖለቲካ መሳሪያ ሆኖ ማገልገሉም የሚካድ አይደለም።

"የፊሽካው ተነፋ " ፕሮፓጋንዳ እና የአማራ ጎበዝ አለቆችን ትግል "የነፃነት ታጋዮች " የሚል የዳቦ ስም አውጥቶ የፈጠራ ታሪክ ሽሚያ ውስጥ ገብቶ የማደናገር ስራ ሲሰራም እናውቃለንና!!!

አሁን ግን ከታማኝ ምንጭ ስለኢሳት የደረሰኝን መረጃ ላጋራችሁ።

ኢሳት ከአየር ላይ የወረደው በገንዘብ
እጥረት አይደለም።

እኛም ከኢሳት የተገለልነው "የፋይናንስ ችግር ገጠመን "በሚል የተንኮል ስራ እንደነበር የሚታወስ ነው።

አሁን ባለው ሁኔታ ለዶር አብይ የለውጥ አስተዳደር ከኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በላይ ትልቁ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ኢሳት ነው።

የዶር አብይ የብልፅግና ፓርቲ ለመንግስት ሚዲያዎች ከሚመድበው በጀት ይልቅ በእጅ አዙርም ቢሆን ኢሳትን ቢደግፍ ይመርጣል።

በተለይ ምርጫው ሲቃረብ ለብልፅግና ፓርቲ ስልጣን መወጣጫ ትልቅ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያ ተደርጎ የሚወሰደው ኢሳት ነው።

በደረሰኝ መረጃ መሰረት አሁን የተፈለገው ኢሳት በተወሰኑ ሰዎች ያጣውን የተዓማኒነት ችግር ለመመለስ ፋይናንስ አጠረኝ በሚል ከለውጡ ሀይል ጋር ግንኙነት የለኝም የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ነው::

ገለልተኛ መስሎ የህዝብን ቀልብ የመሳብ የፓለቲካ ሴራ መወጠኑን ውስጥ አዋቂዎች ያጋሩኝን እኔም ሹክ ልበላችሁ ብየ ነው::

እናም ወገኖቼ እራሳችሁን ከእንዲህ አይነት የፖለቲካ ሴራ ብትጠብቁ መልካም ነው::

እናም ከተወሰነ የፓለቲካ ጨዋታ በኃላ ኢሳት በቅርቡ ወደ አየር ይመለሳልና አትሸወዱ!!!

ኢሳት የብልፅግና አይን እና ጆሮ ነው::
ኢሳት አማራ ጠል ነው!!